


በላቧ ያደረች - ራእይ የተመኘች፣

ካገር ልትገባ - ጎጆ የቀለሰች፣

ጉልበቷን ቸርችራ - ለሌባ ያስረከበች፣

ገንዘቧን ለቃቅማ - ወደ ኢትዮጵያ ልካ፣

ቤት ልትሰራ - ኑሮ ልታሳካ፣

**አንገት ማስገቢያዋን - ካገር ልትሰራ፣**

**በኤርሚያስ አመልጋ - ተወሰደ ብሯ፣**

ሌባው ከወያኔ - አብሮ የሰራ፣

በጠራራ ፀሃይ - በሩ ተከፍቶሎት፣

ካገር እንዲወጣ - ወያኔ ፈቅዶሎት፣

ስንቱን አስለቀስከው - እንባ አሳበስከው፣

ስንቱን ቤት አፍርሰህ - ከመንገድ የጣልከው፣

ፈጽሞ በሰላም - አንተም አትኖርም፣

ሲቃ መከራ ውስጥ - መግባትህ አይቀርም፣

የጥቅም ተካፋይ - ካገር ውስጥ ያላችሁ

እንደዚሁ አይቀርም - ድሃ አስለቅሳችሁ!!

የሰው ባዶ ኤልያስ - የሰው እንኩቶ ነው፣

ኪስ አውላቂ ለባ - የሴይጣን ቁራጭ ነው፣

በኛ ጉያ ገብተህ - ፈጽሞ አትደበቅ፣

አጥብቆ የሚታገል - የሚልክ መቀመቅ፣

ክንዳችን ጠንካራ - ለሌባ የማይመች፣

የሳይንሱ ማደግ - ቀልጣፋ የሚመች፣

የድሃዎቹ ገንዘብ - ባስቸኳይ ይመለስ፣

የድሃዎቹ ገንዘብ - ባስቸኳይ ይመለስ !!

መይሳው!!

የህን ግጥም ለመጻፍ የገፋፋኝ

በኤርሚያስ አመልጋ ምክንያት ችግር ላይ የወደቁ ኢትዮጵያንን አግኝቼ ልቤ ስለተሰበረ ነው፣ ሁለት ህጻናት ልጆች አልዋቸው ፥ ችግራቸውን አስረዱኝና እናት እንባቸውን አፈሰሱት፣ አባት ጠቀርሻ ለብሰዋል። እና አዘንኩና ብ ዕሬን ከወረቀት አገናኘሁት። በግርድና የሰሩ አሽ ከር ሆነው የተጎሳቆሉ ናቸው፣ ከዚህ መከራ ገብተዋል ስለሆነም ኤርምያስ በዶንያ ይዘህ የወጣኸውን ገንዘብ መልስ አትባልግ፣ ኤልያስ ባስቸኳይ በሕግ በላህበት አገር እንድትዳኝ እናደርጋለን።አታመልጠንም።